# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

የዓቢይ ጾም አንደኛው ሰንበት ዘወረደ ይባላል።

ዐብይ ጾም መባሉ መድኃኒታችን ስለጾመው ነው። «ሁዳዴ» ጾምም የሚባለው ሑዳዴ በሚባለው ጥንታዊ የእርሻ መሬት ስም ታላቅነቱን ለመግለጽ ነው። … ሲወርድ ከየካቲት ፪ ቀን ሲወጣም ከመጋቢት ፮ ቀን ጀምሮ እስከ በዓለ ትንሣኤ ዋዜማ ያለው ፶፭ ቀን ዓቢይ ጾም ይባላል።
በዚህ ቀን ስለ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ ወደ ምድር መውረድ የሰው ልጅ በትህትና፣ በፈሪሃ አምላክ ስለመኖር ይዘመራል። የዕለቱም ስያሜ የተወሰደው በዕለቱ ከሚዘመረው የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ነው። ከሰኞ ጀምሮ ጾመ ሕርቃል ይባላል። ሰው ለጾም ልቡን እንዲያዘጋጅ ትምህርት የሚሰጥበት በጾም ወቅት ሊኖረን ስለሚገባ ሕይወት የምንማርበት ሳምንት ነው።

## የዕለቱ ምስባክ

ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት
ወተሐሰዩ ሎቱ በረአድ
አጽንዕዋ ለጥበብ ከመ ኢይትመአጽ እግዚአብሔር

ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ
በረአድም ደስ ይበላችሁ
ተግሣጹን ተቀበሉ ጌታ እንዳይቆጣ
መዝ ፪፥፲፩

ትርጉም፡ ለእግዚአብሔር በፍርሃት በመንቀጥቀጥ ተገዙ። በመገዛታችሁም ደስ ይበላችሁ ዋጋ ያለበት ስለሆነ፤ ከፍቅር በመነጨ ፍርሃት ደስ ይበላችሁ። ለእግዚአብሔርም ተገዙ ጥበበ ወልድን እመኑ ወንጌልን በሠራላችሁ አልተቀበላችሁም ብሎ እንዳይፈርድባችሁ በልጁ እመኑ።

ወንጌል፡ ዮሐ ፫፥፲-፳፭
ቅዳሴ፡ የጌታችን (ነአኲተከ)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት
(ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ)

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ዕብ ፲፫፥፯-፲፯ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ያዕቆብ ፬፥፯ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፭፥፲፫ እስከ ፍጻሜ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

# ፈሪሃ እግዚአብሔር

1) ሥጋዊ ፍርሃት ከኃጢአት በኋላ ተከስቷል፤ በጥላቻና በመንቀጥቀጥ የሚሆነው የውስጥ ፍርሃት ሰው ሕገ አምላክን ሲተላለፍ ተጀምሯል። ይህ ዓቢይ ፍርሃት እና ረድአ ወደ ዓለም ከኃጢአት በኋላ ስለመግባቱ (ዘፍ ፫፥፲ ። ምሳ ፳፰፥፩) ላይ እናነባለን። ክርስቲያን ግን የእግዚአብሔርን ፍቅር ስለሚያውቅ ከእንደዚህ ያለ ፍርሃት በክርስቶስ ነጻ ወጥቷል። (ሮሜ ፰፥፲፭ ። ዮሐ ፬፥፲፰)

2) ፈጣሪን ለማክበር እና በፍቅር ላይ የተመሰረተች ፈሪሃ እግዚአብሔር በኃጢአት ምክንያት ከተፈጠረው ፍርሃት የተለየ ነው። ይህ ፍርሃት ከፍቅር ፣ ከአክብሮት የመነጨ በመሆኑ ለምስጋና ለቅዳሴ የሚያተጋ በመሆኑ በገነት በነበረው ሰው ሕይወት ውስጥ ነበረ። ሰው ይህን ቅዱስ ጸጋ በጠላት ምክር ሲነጠቅ በድፍረት ኃጢአት ሠራ። ፈሪሃ እግዚአብሔር የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ናት (ምሳ ፩፥፯ ። ምሳ ፱፥፲) በመሆኑም ዳዊት ሊያስተምረን ፈቅዶ «ኑ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ላስተምራችሁ» ይላል። (መዝ ፴፫፥፩)

የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ የተባለችበት ምክንያት ሰው እግዚአብሔር ከፈራ እንደ አብርሃም የታዘዘውን ሁሉ ያደርጋል። (ዘፍ ፳፪፥፲፪-፳፫) እግዚአብሔርን ፈርቶ የሠራው ሥራም ሞገስ ይሆዋል። (ዘፍ ፵፩፥፵፪) አባታችን ዳዊት ኑ ላስተምራችሁ ያላቸውን ልጆቹን ሊያስተምር «የእግዚአብሔር መልአክ እግዚአብሔርን በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይከባል፣ ያድናቸውማል» በማለት ፈሪሃ እግዚአብሔር በመላእክተ እግዚአብሔር እንደምታስጠብቀን ተናገረ። (መዝ ፴፫፥፯)

ፈሪሃ እግዚአብሔርም ሕይወትን ለሚፈቅድና በጎን ዘመን ለማየት ለሚወድ ጠቃሚ መሆኑን እያስገነዘበ ሲተረጉም እግዚአብሔርን የምትፈራ ከሆነ በጎ ዘመንንም ለማየት፣ በሕይወት መኖር ከፈለግህ፣ አንደበትህን ከክፉ ከልክል፣ ከንፈሮችህም ሽንገላን እንዳይናገሩ ከክፉ ሽሽ፣ መልካምን አድርግ፣ ሰላምን እሻ ተከተላትም አለ (መዝ ፴፫፥፲፬) በፈሪሃ እግዚአብሔር የተጠመቀው ዳዊት «የሚፈሩት አንዳችን አያጡም ቅዱሳኑ ሁሉ እግዚአብሔርን ፍሩት» አለ ቁጥር ፱። በአሥራ አንደኛው መዝሙሩም «እግዚእብሔርን የሚፈራ ትእዛዙንም እጅግ የሚወድ ሰው ምስጉን ነው ዘሩም በምድር ላይ ኃያል ትሆናለች» አለ ቁጥር አንድ። ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎችም ከደፋሮች ይልቅ ክቡራን መሆናቸውን እነርሱንም የሚያከብር እንደሚከበር ሲናገር «ዘያከብሮሙ ለፈራህያነ እግዚአብሔር» እግዚአብሔርን የሚፈሩትን የሚያከብር ይከብራል። (መዝ ፲፬፥፬) በእግዚአብሔር ድንኳን ያድራል አለ።

ልጁ ሰሎሞንንም እግዚአብሔርን ፍራ፣ ትእዛዛቱንም አክብር (ጠብቅ) አለ። (ምሳ ፳፫፥፯) እግዚአብሔርን የሚፈራው የመቶ አለቃ ጸሎቱ ተሰማለት ለአሚነ ክርስቶስም በቃ (የሐዋ ሥራ ፲፥፪)

አንባቢ ሆይ፡
እንግዲያውስ እኛ ወንጌልን እንዳልተቀበሉ በክርስቶስም እንዳላመኑ ለፍርድ እንደተጠበቁ ሰዎች ከድንጋጤና ከጭንቀት የሚፈጠረውን ፍርሃት አስወግደን (የሐዋ ፮፥፳፱ ። ፳፬፥፳፭ ። ዕብ ፲፥፳፮-፳፯ ። ራዕ ፳፩፥፰) ከዚህ ዓይነቱ ፍርሃት ክርስቶስ ነጻ እንዳወጣን እየተገነዘብን የእግዚአብሔርን ፍቅር ቅድስናና ክብር ታላቅነት በሚገልጸው ፈሪሃ እግዚአብሔር እንቁም።

ቅዱስ ጳውሎስም «በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ» ይላል (ፊልጵ ፪፥፲፪) ቅዱስ ጴጥሮስም «በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃትና በፍቅር ኑሩ» ይላል (፩ኛ ጴጥ ፩፥፲፯) በዕብ ፲፫፥፯-፲፯ ላይ ደግሞ «የማይናወጥን መንግስት ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ጸጋ እንያዝ አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና» ይላል።

በመለኮታዊ ጥባቆቱ ከድፍረት ኃጢአት እግዚአብሔር እንዲያድነን እንጸልይ እንማጸነው (መዝ ፲፰፥፲፫) « … ከእኔም ፈቀቅ እንዳይሉ መፈራቴን በልባቸው ውስጥ አኖራለሁ ለእነሱም መልካም በማድረግ ደስ ይለኛል» ብሎ የነገረውን ተስፋ እንዲያወርሰን (ኤር ፴፪፥፵) ከፍቅር የተነሳ እንፍራው እናክብረው። የአጋንንት ዓይነት ፍርሃት ሳይሆን አባታችን ስለሆነ ክብርን ንጉሣችን ስለሆነ ፍርሃትን ይዘን ለእርሱ በፍቅር እንገዛለት።

«ልጅ አባቱን ያከብራል ባሪያም ጌታውን ይፈራል እኔስ አባት ከሆንኩ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንኩ መፈራቴ ወዴት አለ?» እንዳንባል። (ሚልክያስ ፲፮፥፯)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።